# ፌዴራላዊ ባንሆን ምን እንሆን ነበር?

**ለሚ ዋቄ 05-09-18**

*አሁን ያለውን ፌደራላዊ ስርአትና ባለፉት አምስት ዙር የመንግስት የስራ ዘመን በስልጣን ላይ የቆየውን ኢ.ህአዴግ የሚቃወሙ አንዳንድ ግለሰቦችና ቡድኖች ለተቃውሚቸው የሚያቀርቡት ቀዳሚ ምክንያት ሃገሪቱን በብሄር፣ በዘር፣ በጎሳ ከፋፈለ የሚል ነው። በተለይ ሃገሪቱ በጎሳ ተከፋፈለች የሚሉት ቡድኖች አሁን ያለውን የብሄር ብዝሃነትን የተቀበለ ፌደራላዊ ስርአት አዋርደው ማየት የሚፈልጉ ናቸው። ጎሳ በአንድ ብሄር ወይም ብሄረሰብ ውስጥ ጥብቅ የደም ትስስር ያላቸውን ቤተሰቦች የያዘ አነስተኛ የህብረተሰብ ክፍል ነው። ለምሳሌ በኦሮሞ ውስጥ በርካታ ትላልቅና ንኡስ ጎሳዎች አሉ። ቱለማ፣ ሜጫ፣ ቦረና ባሬንቱ ትላልቅ ጎሳዎች ሲሆኑ በእነዚህ ስር በርካታ ንኡስ ጎሳዎች አሉ። እንደብሄር ግን ሁሉም ኦሮሞዎች ናቸው። አሁን በሃገሪቱ የተገነባው ስርአት ጎሳን ሳይሆን ብሄርን ወይም ብሄረሰብን መሰረት ያደረገ ሆኖ ሳለ በጎሳ የተከፋፈለ አድርጎ ማቅረብ ትልቅ ስህተት ነው። ያም ሆነ ይህ አሁን ያለውን የኢ.ፌዴሪ ስርአትና ገዢውን ፓርቲ ኢ.ህአዴግ ለመቃወም ሃገሪቱን ከፋፈለ የሚል መቃወሚያ የሚያቀርቡ ቡድኖችን ማንነትና የፌደራላዊ ስርአቱን ፖለቲካዊ መሰረት እንመለከት።*

*የኢ.ፌዴሪ ህገመንግስት ወይም ኢ.ህአዴግ ሃገሪቱን በብሄር አልከፋፈሉም። ብሄሮችን ፈጥረው ወይም ከሌላ ቦታ አምጥተው የተከፋፈለች ሃገርን መመስረት የሚያስችል አቅምም የላቸውም። ኢትዮጵያ የምትባለው ምድር ቀድሞውኑም አንድ ብሄራዊ ማንነት ያላት ሃገር አይደለችም። ኢትዮጵያ የኦሮሞ፣ ሲዳማ፣ ሱማሌ፣ ወላይታ፣ አፋር፣ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ወዘተ ብሄሮችና ብሄረሰቦች የሚኖሩባት ሃገር ነች። እነዚህ ብሄሮች በኢ.ህአዴግ ወይም በኢ.ፌዴሪ ህገመንግስት የተፈጠሩ አይደሉም። የነበሩና ያሉ በፈጣሪ የተፈጠሩ ናቸው። እናም የኢ.ፌዴሪን መንግስትና ህገመንግስት እንዲሁም ኢ.ህአዴግን በሃገር ከፋፋይነት መክሰስ መሰረተ ቢስ ነው። ኢ.ህአዴግና በኢትዮጵያ ብሄሮችና ብሄረሰቦች የተዘጋጀው ህገመንግስት በተጨባጭ መሬት ላይ ላሉት ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች እውቅና ነው የሰጡት።*

*አሁን ያለውን የኢትዮጵያን ቅርጽ የፈጠሩት የቀደሙት የነገስታት ዘውዳዊ ስርአት ኢትዮጵያ የብዝሃ ብሄር ሃገር ብትሆንም፣ ይህን ብዝሃነት በአንድ የማንነት መለያ በመጨፍለቅ አሃዳዊ ሃገር የመመስረት ራዕይ ነበረው። ዘውዳዊ ስርአቱ ይህን ራዕይ ለማሳካት ስትራቴጂ ነድፎ ለአንድ መቶ ዓመት ያህል*

ተግባራዊ አድርጓል። ይሁን እንጂ የዚህ ስትራቴጂ ተግባራዊነት የተለያዩ ብሄራዊ ማንነቶችን አጥፍቶ አንድ ብሄራዊ ማንነት ያላትን ኢትዮጵያ መፍጠር አላስቻለም።

አሃዳዊ ስርአት ለመፍጠር በብሄራዊ ማንነቶች ላይ የሚደረገው ጫና እያየለ በሄደበት መጠን የማንነት፣ የእኩልነትና የነጻነት ጥያቄና ትግልም እያየለ ሄዷል። በተለይ ከ1960ዎቹ መጀመሪያ አንስቶ የተቋቋሙት የተለያዩ ብሄራዊ የነጻነት ንቅናቄዎች የዚህ ማሳያ ናቸው። አሃዳዊ ስርአቱን ለመውደቅ ያበቃው ይህ በየአቅጣጫው የተካሄደ የብሄራዊ ማንነት፣ የእኩልነትና የነጻነት የትጥቅ ትግል ነው።

ከዚህ በኋላ ሃገሪቱ ሁለት አማራጮች ብቻ ነበራት። አንደኛው አማራጭ ለብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ማንነት እውቅና ሰጥቶ፣ ራሳቸውን በራሳቸው እያስተዳደሩ እርስ በርስ በመከባበር፣ በእኩልነት የሚኖሩባትን የህዝቦች አንድነት ያላት ኢትዮጵያን መመስረት ነው። ይህ አሁን በስራ ላይ ያለው ፌደራላዊ ስርአት ነው። ሁለተኛው አማራጭ መለያየት ወይም *ማንነታችሁ ተጨፍልቆ አንድ መሆን አለባችሁ* በሚለው ወገንና በነጻነት ጠያቂ ብሄራዊ ንቅናቄዎች መሃከል ጦርነት ሲያካሂዱ መኖር ነበር።

ከእነዚህ ሁለት አማራጮች የተሻለው ፌደራላዊ ስርአት መስርቶ በአንድነት መኖር ነበር። የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው እያስተዳደሩ በእኩልነት የሚኖሩበት ፌደራላዊ ስርአት፣ የኢትዮጵያን አንድነት የሚያጠናክር እንጂ ሃገሪቱን የሚከፋፍል ወይም የመገንጠል ጥያቄን የሚቀሰቅስ አይደለም። የፌደራላዊ ስርአት ግብም የኢትዮጵያን አንድነት በማይናወጥ መሰረት ላይ ማቆም ነው።

ፌደራላዊ ስርአቱ ተግባራዊ በተደረገባቸው ያለፉ ሁለት አስርት ዓመታት በሃገሪቱ ሰላም ሰፍኗል። የብሄራዊ ነጻነት ግንባሮች የትጥቅ ትግል ከጀመሩባቸው ዓመታት እስከ 1983 ዓ/ም ባለው ጊዜ ውስጥ በተለያዩ የሃገሪቱ አካባቢዎች ሰላም አልነበረም። በተለይ ከ1967 እስከ 1983 ዓ/ም የነበሩት አስራ ሰባት ዓመታት ሃገሪቱ በጦርነት ስትታመስ የነበረችበት ወቅት መሆኑ የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው። በእነዚህ አስራ ሰባት ዓመታት መጠናቸው ቢለያይም በሁሉም የሃገሪቱ አካባቢዎች ጦርነት ይካሄድ ነበር። የዚህ ጦርነት መነሻ የነጻነትና የእኩልነት ጥያቄ ነበር። በእነዚህ አስራ ሰባት ዓመታት ከውጭ ጠላት ጋር ጦርነት የተካሄደው ከየካቲት 1969 እስከ የካቲት 1970 ዓ/ም ለአንድ ዓመት ብቻ ነው፤ ከወራሪው የሶማሊያ መንግስት ሃይል ጋር።

ሃገሪቱ በፌደራላዊ ስርአት በተዳደረችባቸው ዓመታት እነዚህ የእርስ በርስ ግጭቶች ከስመዋል። እርግጥ በፌደራላዊ ስርአቱ በብሄር ላይ ተመስርተው ተደራጅተው ብረት ያነሱ ቡድኖች አሉ። እነዚህ ቡድኖች ክልላዊ መንግስታት ስልጣናቸው በቂ አይደለም፤ ከተጸእኖ አልተላቀቁም ወዘተ በሚል ምክንያት ወደትጥቅ ትግል የገቡ ቡድኖች ናቸው። የኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ) እና የኦጋዴን ብሄራዊ የነጻነት ግንባር (ኦብነግን) ለአብነት መጥቀስ ይቻላል። እነዚህ ቡድኖች፣ ቆመንላቸዋል የሚሏቸው ብሄሮች/ብሄረሰቦች በወከሏቸው የራሱ ልጆች ብቻ የሚተዳደር መሆኑ፣ በፌደራል መንግስት ውስጥ በህዝባቸው ቁጥር ልክ ተወክለው ስልጣን መጋራታቸው፣ በአስፈጻሚው አካልም ውስጥ የሚሳተፉ መሆኑ፣ ቋንቋቸው የክልላዊ መንግስታቸው የስራ ቋንቋና የማስተማሪያ ቋንቋ መሆኑ፣ ብሄሮቹ ባህላቸውን እያሳደጉ፣ ታሪካቸውን እየተንከባከቡና ይፋ እያደረጉ መሆኑ፣ ቋንቋቸውና ባህላዊ እሴቶቻቸው በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ደረጃ የሚጠኑ መሆኑ ወዘተ የያዙትን ዓላማ መሰረተ ቢስ አድርጎባቸዋል። በመሆኑም ከጊዜ ወደጊዜ እየተዳከሙና እየተመናመኑ ሄደው ጥቂት ግለሰቦችን ይዘው በውጭ ሃገራት ስማቸው ብቻ የሚጠራ ሆነው ቀርተዋል።

በሌላ በኩል ፌደራላዊ ስርአቱ ሃገሪቱን ለመበታተን አደጋ አጋልጧል በሚል ፌደራላዊ ስርአቱን አፍርሰው አሃዳዊ ስርአት ለመመስረት ወደትጥቅ ትግል የገቡ ቡድኖች አሉ። እነዚህም ቢሆኑ ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደርና የእኩልነት መብታቸው በተረጋገጠላቸው ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች የሚወከሉ ኢትዮጵያውያንን ድጋፍ ማግኘት ስላልቻሉ በትጥቅ ትግል ይህ ነው የሚባል እንቅስቃሴ ማድረግ አልቻሉም። እነዚህ ቡድኖች አሃዳዊ ስርአቱ እንደፈረሰ ህይወት የሚዘሩ ይመስሉ የነበረ ቢሆንም አሁን ከስመዋል።

እነዚህ ከላይ የተገለጹ እውነታዎች ናቸው ባለፉት ሁለት ተኩል አስርት ዓመታት በሃገሪቱ ሰላም እንዲሰፍን ያደረጉት። ይህ ሰላም ደግሞ ህዝበና መንግስት ልማት ላይ የሚያተኩሩበትን ፋታ አስገኝቷል። በመሆኑም በተጨባጭ በህዝቡ ኑሮ መሻሻል የተገለጸ ተከታታይ የኢኮኖሚ እድገት እንዲሁም ትምህርትና ጤና የመሳሰሉ ማህበራዊ ልማቶችንና መሰረተ ልማት ማስፋፋት ተችሏል። ባለፉ ሁለት አስርት ዓመታት በሃገሪቱ የተመዘገበው እድገት የፌደራላዊ ስርአቱ ውጤት ነው ማለት ይቻላል።

ይሁን እንጂ፣ አልፎ አልፎ ከማንነትና ከወሰን ጋር በተያያዘ ግጭቶች የሚነሱበት ሁኔታ አሁንም የታያል። በተለይ የአሃዳዊ ስርአት ተስፈኞች ይህን ከማንነትና ከወሰን ይገባኛል ጥያቄ ጋር ተያይዞ የሚነሳ

አለመግባባትና ግጭት፣ በቀዳሚነት በብሄራዊ ማንነት ላይ የተመሰረተው ፌደራላዊ ስርአት የፈጠረው አድርገው ሲያቀርቡ ይስማማሉ።

በመሰረቱ ህገመንግስታዊው ፌደራላዊ ስርአቱ ምንም አይነት የማንነትና የወሰን ይገባኛል ጥያቄ የማይነሳበት ያለቀለት ስርአት አይደለም። የማንነትና የወሰን ይገባኛል ጥያቄዎች በማንኛውም ጊዜ ሊነሱ እንደሚችሉ ታሳቢ ተደርጓል። እናም ጥያቄዎቹ ሲነሱ ምላሽ የሚያገኙበት ህገመንግስትዊ ስርአት ተቀምጧል። በመሆኑም ጥያቄዎቹ ሲነሱ ወደግጭት ከመሸጋገራቸው በፊት በህገመንግስቱ ምላሽ እንዲያገኙ ይደረጋል። ባለፉት ዓመታት ከማንነትና ከወሰን ይገባኛል ጥያቄ ጋር ተያይዞ ግጭቶች ያጋጠሙት፣ ጥያቄዎቹን በወቅቱ ህገመንግስቱ ባስቀመጠው መሰረት ሳይስተናገዱ በመቅረታቸው ነው። እናም ፌደራላዊ ስርአቱ የእርስ በርስ ግጭት መንስኤ ተደርጎ መወሰድ የለበትም።

እርግጥ በብሄር ላይ የተመሰረተው ፌደራላዊ ስርአቱ በሃገሪቱ ለሰፈነው ሰላምና ለተመዘገበው ልማት እንዲሁም ለሃገሪቱ አንድነት መሰረት ቢሆንም፣ ከጋራ እሴቶች ይልቅ የተናጥል እሴቶች ላይ ትኩረት የተደረገበት ሁኔታ ታይቷል። ይህ የኢትዮጵያዊነት ስሜት በሚፈለገው ልክ እንዳይጎለብት አድርጓል። በመሆኑም ለልዩነት የተሰጠውን ያህል ትኩረት ለኢትዮጵያዊነት የጋራ እሴቶችም መስጠት አስፈላጊ ነው።

በአጠቃላይ፣ ኢትዮጵያ በብሄር ላይ የተመሰረተ ፌደራላዊ ስርአት የመሰረተችው ብዝሃ ብሄር ያላት ሃገር በመሆኗ አንድነቷን ጠብቆ መቆየት የሚያስችል ሌላ አማራጭ ስለሌለ ነው። ለኢትዮጵያ ፌደራላዊ ስርአት የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን የሃገሪቱን አንድነት ለማስጠበቅ በታሪካዊ አስገዳጅ ሁኔታ (historical necessity) የመጣ ነው። ኢትዮጵያ ፌደራላዊ ሳትሆን አንድነቷን ጠብቃ መዝለቅ አትችልም። እናም ፌደራላዊ ስርአቱን ማፍረስ ውጤቱ ሃገሪቱን ማፈረስ ብቻ ነው።